# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"... እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" (ኢሳ 48÷17)

God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 - 9395

ታህሣስ 1995 December 2002 "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፥ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።" (ኢሳ 54÷13)
---------- አ ዘ ጋ ጅ መ ላ ኩ ት ዕ ዛ ዙ -------------

## ብርሃነ ልደቱ



(የብስራቱ ቤተ ክርስቲያን) The church of the annu

"...መልአኩ ገብሪኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ...ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ ÷ የድንግሊቱም ስም ማሪያም ነበረ። ...መልአኩም እንዲህ አላት፡- ማሪያም ሆይ÷በእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም÷ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ÷ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል÷ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፥ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ÷ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም። ማሪያምም መልአኩን፡- ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል ÷ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል፥ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።" (የሉቃስ ወንጌል 1÷26-28 ፤ 30-35)

ከዚህ በላይ በቅድስት ማሪያምና በመልአኩ ገብሪኤል መካከል የተደረገው ንግግር ÷ ይህ ቤተክርስቲያን በተሠራበት ሥፍራ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ፡- (እስራኤል) በናዝሬት ገሊላ ከተማ ነው። (ዘ ቸርች ኦፍ ዘ አነንሲየሽን) የተባለበትም ምክንያት የአዳኝ መፀነስ÷ ብስራት የተነገረበት ሥፍራ በመሆኑ ነው።

ክሪስማስ Christ-mass የክርስቶስ (ልደት) መታሰብያ በዓል ነው። በሚሊዮን የሚቆጠሩ የዓለም ሕዝብ ያከብሩታል። እያንዳንዱ ሰው በተለያየ ምክንያት ያከብረዋል። ጌታ ኢየሱስ ሰውን ለመታደግ ሥጋ ለብሶ ወደ ዓለም የመጣ አምላክ መሆኑን በመረዳት የሚያከብሩ አሉ። እነዚህ ደኅንነትን ቀምሰው አዳኝነቱን ስለተረዱ፡- በአድናቆት የሚያከብሩ ናቸው። ወላጆቻቸውን ወይም ጎረቤታቸውን በመከተል ለባሕል ያህል የሚያከብሩም አሉ። ለምሳሌ በአውሮጳና በምዕራብ ሐገሮች የኢየሱስ ስም አንዴም ሳይጠሩ በዓሉን የሚያከብሩ አሉ። ገናናው የክሪስማስ ቅርሳቸው፡- የጥድ ዛፍ÷ ዕውቁ ስም ደግሞ (ሳንታ ክላውስ) የተባለው አውሮጳዊ ሽማግሌ ነው። ምንም እንኳ በምዕራቡም ሐገሮች በዕውቀት የጌታን ቀን የሚያከብሩ ብዙ ሰዎች ቢኖሩም÷ ብዙዎች ግን ያለ ዕውቀት ያከብሩታል። ይነግዱበትማል።

ይህን ካልን ዘንዳ፡- የጌታ ኢየሱስን ልደት (ክሪስማስን) ማክበር የሚገባው እንዴት ነው? የሚል ጥያቄ ማንሣት ይኖርብናል። የጌታን ልደት ብቻ ሳይሆን ሞቱንም÷ትንሣኤውንም÷ዳግመኛ ምጽአቱንም፡- ብናስብ ጌታ በጣም ደስ ይለዋል። ምክንያቱም በሉቃስ ወንጌል 22÷19 "እንጀራንም አንሥቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸውና፡- ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፥ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።" የሚለው፡- መታሰቢያ የሚቀበል የሚወድም መሆኑን ስለሚያረጋግጥ ነው። እንዲህም ከሆነ ለእግዚአብሔር መታሰቢያ ማድረግ ተገቢና አስፈላጊ ነው፥ ማለት ነው።

መታሰቢያ የሚደረገው ላዩት÷ለሰሙት ወይም ለተለማመዱት ነገር ነው። የሚታሰበው ነገር ከመታሰቡ አስቀድሞ መታወቅ አለበት ማለት ነው። ስለዚህ ዓለም ሁሉ የሚያከብረውን የልደቱን በዓል በአግባቡ መረዳት እጅግ ጠቃሚ ነው።

# ልደቱን ማክበር

የጌታ ልደት በዓለም ታሪክ ተወዳዳሪ የሌለው መሆኑን ለማረጋገጥ ብዙ ማስረጃ አያስፈልግም። በአብዛኛው የዓለም ሐገሮች የዘመን አቆጣጠር የሚጀምረው ከጌታ ልደት መሆኑ በቂ ነው። ከጌታ ልደት ወዲህ ያለው ዘመን÷ዓመተ ምሕረት ወይም (አኖ ዶሚኒ) ማለትም የጌታችን ዓመት ይባላል። ላመኑትም ለማያምኑትም የሰው ልጆች ታሪክ በዚያ ቀን ተለውጧልና።

መጽሐፍ እንደሚል፡- ዓለም በተፈጠረበት ጊዜ "እግዚአብሔር አምላክም በምሥራቅ በዔድን፥ ገነትን ተከለ፤ የፈጠረውንም ሰው ከዚያ አኖረው።" (ኦሪት ዘፍጥረት 2÷8) ሴይጣንም ሔዋንን አስሳተ። አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ተላለፉ። "...እነርሱም ዕራቁታቸውን እንደ ሆኑ አወቁ ..." "...አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ።" (ሮቅሪት ዘፍጥረት 3÷7 እና 8)

በዚያን ጊዜ የተፈጠረው ከእግዚአብሔር መለየት ለረዥም ዘመን በሰው ላይ ኖረ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ከምሕረቱ የተነሣ÷በታቦት አማካይነት በሕዝቡ መካከል ለማደር ቢፈቅድም÷ወደ ክብሩ ታቦት መቅረብ ለካሕናት እንኳ ሳይቀር ያስፈራ ነበረ። በብሉይ ኪዳን የነበረው የኃጢአት መስዋዕት ለኃጢአታችን ዘላቂ ካሳ መሆን ስላልቻለ ነው። የመጽዳቱ÷ በሕያጽ መርጨቱና የእንስሳቱ ደም ሥርዓት ሁሉ ብቁ ሳይሆን ቀርቶ ካሕናት እንዳይቀሰፉ ጥንቃቄ ይደረግ የነበረው ለዚህ ነው። (ለምሳሌ በልብሰ ተክሕኖው ዘርፍ ቃጭሎች÷በካሕኑ እግር ደግሞ ገመድ ይታሰር ነበረ።) ከካሕኑም በቀር ማንም ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ መድረስ አይችልም ነበረ።ምክንያቱም ኃጢአት ወደ ቅድስናው ይጠጋ ዘንድ ስለማይችል ነው። ነገር ግን ከዘመናት በኋላ "የሴቲቱ... ዘር" የተባለው ኢየሱስ ተወለደ። (ዘፍጥረት 3÷1) በአደገና ምድራዊ ኃላፊነቱን በፈጸመ ጊዜ እንደ ተጻፈለት ለቅሰዋዕት ራሱን ሰጠ። መጽሐፍ እንዲህ ይላል፡- "ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ።" "እነሆም የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፥ምድርም ተናወጠች ዓለቶችም ተሰነጠቁ÷መቃብሮችም ተከፈቱ÷ተኝተው (ሞተው) ከነበሩትም ቅዱሳን ብዙ ሰዎች ተነሡ፥ ከትንሣዔውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ (ኢየሩሳሌም) ገቡና ለብዙዎች ታዩ።" (የማቴዎስ ወንጌል 27÷50-54)

"የቤተ መቅደስ መጋረጃ" የተባለው ሕዝቡንና የክብሩን ታቦት የሚለያይ ግርዶሽ ወይም ግድግዳ ነው።ይህም ግርዶሽ ኃጢአት ባይኖር ኖሮ ባላስፈለገም ነበር። ወይም ሰው ስለ ኃጢአቱ በቂ መስዋዕት ማቅረብ ቢችል ኖሮ ባላስፈለገ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ተወልዶ ኃጢአት ያልተገኘበትን ነፍሱን በመስቀል ላይ በሰጠ ጊዜ ግን መጋረጃው ተቀደደ። እግዚአብሔር ይመስገን። የሰው ልጆችን ሁሉ ዕዳ ለመሸፈን የሚችል ዋጋ ተገኘ። እርሱም ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት÷በዚህ ወር ገደማ÷የዳዊት ዘር ከሆነችው ከድንግል ማሪያም የተወለደው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ብርሃነ ልደቱም ታሪካዊ ብቻ ሳይሆን ዘላለማዊም ነው። ከቀድሞ በእግዚአብሔር ዘንድ የታሰበ ስለ ሆነ ዘላለማዊ ነው። የዓለምን ታሪክና ሂደት ስለ ለወጠ ታሪካዊ ነው። ስለዚህ በተመረጠና በተወደደ አኳኋን መታሰብና መከበር ይገባዋል።

☞ **በዕምነት ማክበር፡-** "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ÷ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና።" (የዮሐንስ ወንጌል 3÷16-17)

☞ **በመታዘዝ ማክበር፡-** "በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ÷ ጌታ ሆይ÷ ጌታ ሆይ÷ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም። ... ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።" (የማቴዎስ ወንጌል 7÷21 እና 24)

☞ **በፍሬ ማክበር፡-** "ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ አባቴ ይከብራል።" (የዮሐንስ ወንጌል 15÷8)

☞**በእርሱ ባለማፈር ማክበር፡**–"በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ÷የሰው ልጅ በክብሩ በአባቴና በቅዱሳን መላእክቱ ክብርም ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል፡፡" (የሉቃስ ወንጌል 9÷26)

☞**በምስክርነት ማክበር፡**– "ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ፡፡" (የማቴዎስ ወንጌል 10 ÷ 32 – 33)



መድሃኔ ዓለም ጌታ ተወልዶአል

መልካም የልደት በዓል

"ሕፃን ተወልዶልናልና÷ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፡አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፡ ስሙም ድንቅ መካር÷ኃያል አምላክ÷የዘላለም አባት÷የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፡፡" (ትንቢተ ኢሳይያስ 9÷6–7)

ከአዕላፋት መላዕክቱ ጋር በክብር እስኪመለስ ድረስ፡– የልደቱ÷የተዓምራቱ÷የሞቱ÷የትንሣኤውና የዳግመኛ መምጣቱ መታሰብያ ዘወትር ከልባችን አይጥፋ! የጌታችን መገለጽ ቀርቦአልና!

(በግንቦት 1993 May 2001 መልዕክታችን ክርስትና በሚል ርዕስ ካተምነው ግጥም ስለ ልደቱ የሚያወሳ ክፍል፡–)

## ክርስትና....

የድንግል መፀነስ በትንቢት ሲነገር
ሊወጣ እንዳለው ከእሴይ ግንድ በትር
በእግዚአብሔር መንፈስ በጥበብ ተመልቶ
ዘሩን ከውድቀቱ በራሱ ደም ዋጅቶ
በታላቅ መታዘዝ አብን አስደስቶ
ስለ ብዙዎች ኃጢአት በመስቀል ላይ ሞቶ
ሰውን ወደ ቀድሞው ክብሩ የሚመልስ
የዘመናት ሚስጢር ኢየሱስ ክርስቶስ ፡፡

ድንግልም ወለደች በዳዊት ከተማ
ድንቅና ተዓምራት በእስራኤል ተሰማ
ለምጻሞች ነፁ አሉ ÷ ለእውራንም በራ
አማኑኤል ባሉት የዕብራውያን አውራ
እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚባል ተወራ ፡፡
የአምላካችን ማዳን በዓለም ሁሉ ናኘ ፤
ለተቅበዘበዙት እረኛ ተገኘ ...

# ከመንፈሳዊ ወደ ቁሳዊ

ሰው ሁሉ በምድራዊ ዘመኑ በአንድ ወይ በሌላ መልክ መሻት ሳይኖረው አይቀርም፡፡ የሥራ÷የመኖሪያ ቤት÷የትዳር÷የጡረታና የመሳሰሉትን መሻት ሊኖረን ይችላል፡፡ አማኞችን በዚህ ዓለም ኑሮአችን የሚያስፈልገንን አስመልክቶ የእግዚአብሔር ቃል በፍልጵስዩስ 4÷19 "አምላኬም እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል፡፡"የሚለው፡–እንደ ማንኛውም የእግዚአብሔር ቃል የታመነ ነው፡፡ ይህም ማለት እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ሊሰጠን የሚወድድና የሚችል መሆኑን ማመንና መለማመድ አለብን ማለት ነው፡፡ በረከትና በጎ ስጦታ ሁሉ የሚመጡት ከሰማይ አምላክ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለ ሆነ፡– ሰማያዊው በረከት በምድር ላይ ሊጠቅም በሚችል መልክ እየተመነዘረ፡– "...የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል፡፡" የሚለው ይፈጸማል፡፡ እዚህ ላይ ግን "የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ" እንጂ ያሰኛችሁን ሁሉ እንደማይል እናስተውል፡፡ ሰማያዊው በረከት ግን በምድር ላይ ሊጠቅም በሚችል አኳኋን መቅረብ አለበት፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው በኪሱ በርካታ የኬንያ ገንዘብ ይዞአል እንበል፡፡ ይህ ሰው አዲስ አበባ ምግብ ቤት ገብቶ ወዳጆቹን ቢጋብዝ÷ ምንዛሬ ካላገኘ በክፍያው ወቅት ብዙ ችግር ያጋጥመዋል፡፡ ምክንያቱም በሺህ የሚቆጠር የኬንያ ሽልንግ በአዲስ አበባ ምግብ ቤቶች አንድ ፊንጃን ቡና እንኳ ላያጠጣ ስለሚችል ነው፡፡ ገንዘቡ የዕውነት ገንዘብ ሳይሆን ቀርቶ አይደለም፡፡ ነገር ግን የሌላ ሐገር ገንዘብ ስለ ሆነና በሕጉ መሠረት÷ በተገቢውም መንገድ÷ አስቀድሞ መመንዘር ስላለበት ነው፡፡ የሰማያዊውም በረከት አሠራር ከዚህ ጋር ይመሳሰላል፡፡ ወደ አለንበት ሁኔታ ወይም አኳኋን መመንዘር ወይም መለወጥ ያስፈልገዋል፡፡ የሚመነዘረውም የሰጪውን የመስጠትና የመቀበል ሕግ በተከተለ መንገድ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይህንንም በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ መመሪያዎችን ይሰጠናል፡፡

**<u>መስጠትና መቀበል</u>፡**– "ስጡ ይሰጣችሁማል፤በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና÷ የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መስፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል፡፡" (የሉቃስ ወንጌል 6÷38) እግዚአብሔር ከእርሱ ከተቀበልነው አነስተኛውን ክፍል መልሰን በአሥራት÷ በመባና በምጽዋት መልክ እንድንሰጥ ያዘናል፡፡ ይህንንም የሚያደርግበት ምክንያት ከእኛ ተቀብሎ ታላቅ ነገርን ሊሠራበትና፡– የክቡር ሥራው ተካፋይነትን ዕድል ሊሰጠን ነው እንጂ የሁሉ ፈጣሪ ርዳታችን አስፈልጎት አይደለም፡፡ ለምሳሌ በዮሐንስ ወንጌል 6÷ 9–11 እንደ ተጻፈው፡– ጌታ የአንዱን ወጣት አምስት የገብስ እንጀራና ሁለት ዓሣ ከተቀበለ በኋላ አምስት ሺህ የሚያህል ሕዝብን የመገበበትን ተዓምራት አደረገበት፡፡ ይህም ከአንድ ወጣት የዕለት ምሣ የማይተርፍ ለጌታ የቀረበ ስጦታ÷እግዚአብሔርን የሚያስከብር ÷ ሰጪውንም የሚባርክ የዘላለም ሥራ መሣሪያ ሆነ፡፡

**<u>በመስጠት የሰማይን መስኮት ማስከፈት</u>፡**–"በቤቴ ውስጥ መብል እንዲሆን አሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አግቡ÷የሰማይንም መስኮት ባልከፍትላችሁ÷ በረከትንም አትረፍርፌ ባላፈስላችሁ በዚህ ፈትኑኝ÷ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡" (ትንቢተ ሚክያስ 3÷10) የሰማይ መስኮት ሲከፈትልን፡– መንፈሳዊ መገለጥ÷የአእምሮ አስተዋይነትና እግዚአብሔርን በጥራት ለመስማት የሚያስችል የልብ ጥራትን እናገኛለን፡፡ እግዚአብሔርንም በጥራት ከመስማት በሥጋዊና በመንፈሳዊ ነገሮች ሁሉ እንደ ፈቃዱ በሙላት መባረክ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም እግዚአብሔርን ለሚሰሙት በሚያስፈልጋቸው መሠረትና መጠን÷ መልካም መፈለግንና ጠቃሚ ሃሳብን እንዲሁም አስፈላጊውን ጥበብ ለልባቸው ስለሚናገር ነው፡፡ በእኛ ውስጥ ያስቀመጠው ስጦታና ችሎታ÷ ፍሬያማ ይሆናል፡፡

**<u>ታምኖ መስማራት</u>፡**– የሰማይ መስኮት ሲከፈት የምናገኘው ማንኛውም ራዕይ ሆነ በረከት ጌታ ለሕይወታችን ያለውን ዕቅድ ለመወጣት እንዲያስችለን ሆን ተብሎ ወደ እኛ የሚላክ ስለ ሆነ በጥንቃቄና በዕምነት መጠበቅ አለበት፡፡

**<u>የማያቋርጥ በረከት</u>፡**– በረከት ሁሉ የሚገኘውና የሚጸናው እግዚአብሔርን በመታዘዝ ነው፡፡ ስለ ሆነም ከአንዱ መታዘዝ ወደ ሌላ በምንጓዝበት መጠን እግዚአብሔር መንፈሳዊ ሆነ ቁሳዊ በረከትን በተከፈተው መስኮት ያለማቋረጥ ያፈስስልናል፡፡

**<u>የጴጥሮስ መታዘዝና መባረክ</u>፡**– በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 5 እንደምናነበው፡– ጌታ ለአገልግሎቱ ያስፈለገውን የጴጥሮስን ጀልባ ለመጠቀም ጠየቀው፡፡ ጴጥሮስም ሳያቅማማ በመታዘዝ ፈቀደለት፡፡ ጴጥሮስ በጀልባው አማካይነት ዓሣ በማጥመድ የሚተዳደር ስለ ነበረ÷ የተጠየቀው መተዳደሪያውን ሁሉ ነበረ፡፡ ሆኖም በመታዘዝ ለጌታ አሳልፎ ከሰጠ በኋላ÷ ጌታም በጀልባው ከተገለገለ በኋላ÷ ለጴጥሮስ ቃል መጣለት፡፡ ቃሉም "ወደ ጥልቁ ፈቀቅ በል፤ መረቦቻችሁንም ለማጥመድ ጣሉ" የሚል ነው፡፡ (የሉቃስ ወንጌል 5÷4)ቃሉ የመጣለት ምክንያት ጴጥሮስ በጌታ አገልግሎት ላይ በታማኝነት ዋጋ ስለ ከፈለ÷ ከንብረቱም ሁሉ የበለጠውን (ጀልባውን) ለመስጠት ስላልተቆጠበና ሰማያዊው መስኮት ስለተከፈተለት ነው፡፡ ሌላም ሁለተኛ ጀልባ የሞላው የዓሦች ብዛት የተገኘው በመለኮታዊ አሠራር እንጂ በተለመደ አሠራር አልነበረም፡፡ ምክንያቱም "አቤቱ ÷ ሌሊቱን ሁሉ አድረን ስንደክም ምንም አልያዝንም ነገር ግን በቃልህ መረቦቹን እጥላለሁ" (ሉቃስ 5÷5) ሲል ጴጥሮስ ራሱ ስለሚመሰክር ነው፡፡ ጴጥሮስ ግን በኢየሱስ ቃል መሠረት መረቡን በዘረጋ ጊዜ በጀልባው ሙሉ፡– "የተጨቆነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም" በረከት ተቀበለ፡፡ እንግዲህ አንተም እንዲሁ አድርግ! አንቺም!

------ (ከሁለት ዓመት በፊት መልዕክታችን የተደገመ)



እንኳን ለበዓለ ልደቱ አደረሳችሁ

-- መለኩ (ማሞ) ትዕዛዙ ----------------------------------

## ኢየሱስ ጌታ ነው፡፡ ጌታ ይባርክህ፡፡